# ግልጽ ደብዳቤ

## ለኢትዮጵያ መከለከየ ሰራዊት ባለህበት
## ወንድም የኢትዮጵያ ወታደር
## በተለይ ለአዲሱ ትውልድ)

ጌታቸው ጋረደው

በአገራችን ዘመናዊ የመከላከያ ሰራዊት የተጀመረው ከጠላት ወረራ በፊት በ 1927 ሲሆን በመጀመሪያ የቤልጂግ አሰልጣኞች ስልጠናውን እንደጀመሩ በ 1928 የጣሊያን ፋሽሽቶች አገሪቱን ስለወረሩ የሰለጠኑትን ወታደሮች ጣሊያን ሲገላቸው ያመለጡት ከጥቁር አንበሳ ግንባርጋር ተቀላቅለው ከፍተኛ ግዳጅ ፈጽመዋል። ከነጻነት መመለስ በኋላ በ 1927 የተጀመረው የወታደር ሰለጠና በእንግሊዞች አሰልጣኝነት ሲቀጥል ከጥቂት አመታት በኋላ አገር በቀል አሰልጣኞች በብዛት ስለተገኙ፤ በተጨማሪም የአሜሪካ አሰልጣኞች ከዘመናዊ መሳሪያ ጋር ስለመጡ የሀረር የጦር አካዳሚ ተመሰረተ። ንጉስ ሀይለ ስላሴ በወታደሩ መሰልጠን በደሰቱም በሌላ በኩል ጦር ሰራዊቱ አንድ ቀን ቢያምጽ ከዙፋኑቸው እንደሚያባርራቸው ስለተረዱ፤ ከጦር ሰራዊቱ አሰልጣኝና ተራ ወታደሮች አሰባስበው የክብር ዘበኛ በሚል ስም የሳቸውን ልዩ ጠባቂዎች አቋቋሙ፤ የክብር ዘበኛው አደረጃጀት በአጭር ጊዜ ውጤት ስልአሳየ ንጉሱ የነበረባቸው ስጋት ስለተቀነሰ፤ በሁለቱ ወታደሮች መካከል መልካም ንኙነት እንዳይፈጠር የክብር ዘበኛን አለባበስና ትጥቅ ከጦር ሰራዊቱ የተሻለ ስለአደረጉት መቀናናትና አለመግባባት ስለተፈጠረ ንጉሱ ለጉብኝትና ለስራ ጉዳይ ያለስጋት መንቀሳቀስ ጀመሩ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ንጉሱ ሁለቱን ወታደሮች ወደሚያስፈልግበት ስፍራ በማዘዋወር እንደፈለጉት ሲያዙት ጦር ሰራዊቱ ወሰን ለመጠበቅ፤ በየጠረፉ እንዲዘዋወር ስለአደረጉት ወታደሩ የበለጠውን ጊዜ ከቤት ሰቡ ተለይቶ በየበረሀው ሲንከራተት በወባና በሌላ በሽታዎች ሲሰቃይ ይህንን ችግር ለማስወገድ ንጉሱ ያደረጉት መሻሻል አልነበረም። የጦር ሰራዊቱ ሲመሰረት የተሰጠው የወር ደመወዝ አስራ ስምንት ብር ብቻ ሲሆን በልዩ ልዩ ምክንያት ተቆራርጦ በእጁ የሚገባው ገንዘብ ከአስራ ሁለት ብር አያልፍም። ይህም ሆኖ ዎታደሩ ወሰኑን ሳያስደፍር ሌትና ቀን ጠብቆ የአገሪቱን ህልውና ሲያስከብር፤ ንጉሱ በማመስገን ፈንታ ወታደር ግዴታውን አነደፈጸመ ይቆጥሩት ነበር። የክብር ዘበኛው በንጉሱ አካባቢ ስለኖረ፣ ቤተ መንግስት ውስጥ በከንቱ የሚባክነውን ቢሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለወታደሩ ገቢ ማሻሸያ እንዲሆን ጠይቆ ነበር፤ ግን በጦር ዘራዊቱ የነበሩ ከፍተኛ መኮንኖች ጀነራል መርድ መንገሻና ሌሎች ስለተቃወሙ በረሀ የነበረው ወታደር በየቀኑ በብረት ምጣድ የሚጋግረው ጥቁር ቂጣ ተበልቶ የሚያጠግብ ሳይሆን ነፍስን ለማቆየት የሚጎረስ ነበር። የሱማሌ ወታደሮች ምግብ ከኛዎቹ በጣም የተሻለ ነበር። በተቃራኒ የጦር ሰራዊቱ ከፍተኛ መኮንኖች ኪሳቸው ባዶ ሲሆን ምክንያት ፈጥረው ከሱማሊያ ጋር ጦርነት በመከፈት ለስንቅ ለቤንዚን ለማጓጓዢያ ለዚህና ለዚያ ጉዳይ መግዢያ ብለው ገንዘብ ከግምጃ ቤት አውጥተው ከተከፋፈሉ በኋላ ጦርነቱ ተፈጸመ ብለው ይመለሳሉ። ይህንን ምስክርነት የምሰጠው በመስማት ብቻ ሳይሆን ከ 1953-1958 ሞቃዲሾ በስደት በኖርኩበት ጊዜ በአይኔ ያየሁት ምስክርነት ነው። የመከላየያ ሰራዊቱ የመሪዎች መጠቀሚያ ማስፈራሪያ ሆኖ የኖረው፤ እምቢ አሻፈረኝ ሳይል የተገዛው፤ ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ የመጣ ድክመት፤ እስከዛሬ ያልተለወጠ መሆኑን በመለስ ዜናዊ መንግስትም ያየነው ስለሆነ፥ በወቅቱ ያለው ወታደር ምን እንደሚሰራ በጥቂቱ እንነጋገርበት።

ውድ የኢትዮጵያ ወታደር..... ከዚህ በላይ ያነበብከው ታሪክ አባቶችህ ያለበቂ ክፍያ ለንጉስ ሀይለ ስላሲ ታማኝ አገልጋይ በመሆን፤ ህዝቡ በንጉሱ ላይ ሳያምጽ ማስፈራሪያ ጨካኝ ቀጭ ሆነው እንደ አገለገለት ሁሉ፤ አንተም የዛሬው ትውልድ ወታደር፤ የመለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይ በመሆን ለአስራስ ምንት አመታት

በታማኝነት ስለአገለገልክ፤ አገርህና ህዝብህ ዛሬ ላሉበት ስቃይና ችግር በሽታና ረሀብ ብሶትና እንግልት፤ አንተ ወጣቱ ወታደር ከፍ ያለ አስተቃጽኦ አድርገሀል። መለስ ዜናዊ በሻቢያ ድጋፍ በአኤግ ትብብር በ1983 ኢትዮጵያን በወረረ ማግስት በለበስከው የውስጥ ሱሪ ብቻ ያለ ጫማ ከአስመራ ተባረህ ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ፤ መለስ መጠጊያ ስለአላዘጋጁ በየሜዳው እንድትወድቅ ስለአደረገ የተሸለምከውን ሊሻንና መዳሊያ መሬት ላይ ደርድረህ ተመጽዋች መህን ተገደድህ፤ ያለአንዳች የህይወት ዋስትና ስለተባረርህ አንተ ራስህን ለመርዳት ስለአልቻልክ ባለቤትህና ልጆችህ ጊዜ ለሰጣቸው ጌቶችና እመቤቶች አሽከርና ገረድ መሆን ተገደዱ። በዚህ አይነት ችግር ለአመታት ከተሰቃየህ በኋላ፤ መለስ ከኢሳይያስ ጋር የጀመረው አፍላ ፍቅር አልቆ ፍጥጫ ስለጀመሩ፤ ኢሳይያስ በማን አለብኝነት ኢትዮጵያን ሲወር፣ መለስ ዱብ እዳ ሆነብኝ ብሎ ወረራውን ተቀብሎ ሲቀመጥ፤ ኢሳይያስ በፉከራና በሽለላ ማን ደፍሮኝ በማለት አገርህን ስለወረረ አንተ የተባረርከው ወታደር ከወደቅህበት ተሰብስበህ የሻባያን ወረራ እንድትቋቋም ስልተጠየቅህ በአጭር ጊዜ ወራሪን አባረህ የተወረውን ግዛት አስመለስክ። መለስ ለሻቢያ የሸለመውን የባህር ወደብህን አሰብን ለመያዝ ገስግሰህ ሰላሳ ሰባት ኪሎ ሜትር ሲቀርህ፤ መለስ በጠቅላይ ጦር አዛዥነቱ አሰብን እንዳትይዝ፤ ወደኋላ እንድታፈገፍግ ስለአዘዘህ ተገደህ ወደኋላ ስትመለስ፤ የሻቢያ ወታደር ከጀርባህ መጥቶ እንዲያጠቃ በመደረጉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወንድሞችህ በከንቱ ሞቱ፤ መለስ ዜናዊ ኤሬትራን ለመርዳት አንተ ኢትዮያዊውን ወታደር የኤሬትራ ሰለባ እንድትሆን ከአንተ ጀርባ ከሻቢያ ጋር ስለተስማሙ ታላቅ የአገርና የወገን ክህደት ወንጀል ተፈጸመብህ፣ የመለስ ወንጀል በዚህ ብቻ አልተገታም፤ መለስና ኢሳይያስ የአሰብ ወደብ የኤሬትራ ይዞታ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ባድሜን ለኤሬትራ ለመስጠት፤ ከኢሳይያስ ጋር በምስጢር ባደረጉት ስምምነት ሁለቱ አልጀሪያ ከተማ ተገናኝተው ሲፈራረሙ መለስ ሳይጠየቅና ሳይገደድ የወሰኑ ጉዳይ በፍርድ ቤት ከተወሰነ፣ ያለይግባኝ ተቀብዬ በተግባር አውልለሁ በማለት ቃል ሲገባ ስለስምምነቱ የኢትዮጵያ ምክር ቤት ውይም የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። በመለስ ዜናዊ ስህተት የአንተ ወንድሞች ትርጉም ለሌለው ጦርነት መስዋእት ሲሆኑ፤ አንተም የድካምህ ዋጋ አልተከፈለህም። በንጉስ ሀይለ ስላሴ ዘመን አባቶችህ ደማቸውን ከማፍሰስ ህይወታቸውን ከመሰዋት ሌላ ያገኙት ነገር እንደሌለው ሁሉ የአንተም እድል እንደ አባቶችህ ነው። አንድ ዜጋ ለአገሩ ብሄራዊ ግዴታውን ሲፈጽም ብሄራዊ ጥቅም ለማግኘት ብሄራዊ መብት ሴላለው መብትህን ማስከበሩ የአንተ የወታደሩ ፈንታ ነበር፣ ባድሜ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለኤሬትራ እንዲሰጥ ስለወሰነና መለስ አሻፈረኝ ስላለ መቶ ሺህ ወታደሮች ባድሜ ላይአስፍሯል

ባለፈው ጦርነት ትርጉም ለሌለው ውጊያ እንደ ወንድሞችህ ወደጦርነቱ ሄደህ ለመሞት ስግጁ ነህ ወይስ ይህ የኔ ጦርነት አይደለም ብለህ ታምጻለህ? ለመለስ ዜናዊ ጥቅም ባድሜ ሄደህ ብትሞት ሽልማት ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ስለሚረግምህ፤ የኢትዮጰያ መቃብር ስለሚተፋህ ከሞትክ በኋላም እረፍት አታገኝም። መለስ ዜናዊ አገሪቱን እንደግል ንብረት ይዞ በህዝቡና በአንተ በወታደሩ የወደፊት እድል የሚወስነው እሱ ስለሆነ፣ ህዝቡ በእጁ መሳሪያ ስለሌለው አንገቱን ደፍቶ መገዛት ሲገደድ አንተ ወታደሩ ምን ታደርጋለህ? የህዝቡን መብት ማስከበር የአንተ ፊንታ ቢሆንም እኳንስ ህዝቡን ራስህን ከጥቃት ለመከላከል አልቻልክም። መለስ ለጋሽ አገሮችን አታሎ ገንዘብ ለማግኘት ዴሞክራት መስሎ ለመታየት፤ ህዝቡ በምርጫ የፈለገውን ለመምረጥ ይችላል ብሎ ስለአወጀ፤ ምርጫው ተካሂዶ ተቃዋሚዎች አሸነፉ፣ ግን መለስ አጭበርብሮ አሸንፌያለሁ ስላለ በምርጫው ምክንያት ወጣቶች ባደረጉት ስልፍ አጋአዚ የሚባል ጦር መለስ አዘጋጅቶ አንድ መቶ ዘጠና ሶስት ወጣቶች በመለስ ትእዛ ሲገደሉ፤መለስ በሰጠውመግ ለጫ፣ ወጣቶቹ በወታደሮቹ ላይ ድንጋይ ስለወረወሩ የወተደሮቹን ደህንነት ለማስከበር

ጥይት እንዲተኮስ አዝዢያለሁ፣ ይህም ትክክል ነው በማለት ነፍሰ ገዳይነቱን ራሱ አረጋግጧል፣ ይህ ሁሉ ሲሆን አንተ ወታደሩ ድምጽህን አላሰማህም። አግአዚ የሚባሉት የመለስ ልዩ ወታደሮች በጣም ጨካኞች ሲሆኑ የሚተኩሱት ግንባር ላይ ብቻ ስለሆነ፤ መለስ በኢትዮጵያውያን ላይ ባላው ጥላቻ እነዚህን አግአዚያን ጉግ ሜንጉግ) የሚባሉ አውሬዎች አሰልጥኖ ልጆቻችንን ሲፈጅ፣አንተ የኢትዮጵያ ወታደር ምን ትጠብቃለህ? ወላጅ እናትህ ሁለት ልጆቿ ተገለውባት ሰውነቷ በደም ተለውሶ እንባዋን ስታነባ፤ ገዳዩን ወይም አስገዳዩን ተከትለህ አጸፋውን በማስከፈል ፈንታ እንደሚቾቹ እናት ማልቀስ አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር የሚያደርገው ነገር ነው? የራስህ ወኔ ቢጠፋ እንኳን፤ የልጆቹን ደም ስታይ፤የእናቲቱ ተንሰቅሴቃ ማልቀስ፤አንጀትህን በልቶት ያለተግባር በመቅረትህ በጣም ታዝበነሃል፣ ወንድም የኢትዮጵያ ወታደር እባክህ አንድ ጥያቄ እንጠይቅህ፣ በጀርባዋ ውሀ የተሞላበት እንስራ፤በክንዶቿ አንተንና እህትህን አቅፋ ያሳደገች እናትህ፤ በጸሀይና በብርድ ጠፈር ቀንበር ተሸክሞ ያፈራውን ሰብል ለመንግስት ግብር ከፍሎ በተረፈው ገንዘብ እንድትማር የረዳህ አባትህ፤ ከአስረኛ ግፍል ተባሮ ጎዳና ዳዳሪ የሆነው ትንሹ ወንድምህ፤ ትምህርቱን ጨርሶ ስራ በማጣት አደገኛ ቦዘኔ የሚባለው ትልቁ ልጅህ፡ የመኖር ዘዴ መንገዱ ጠፍቷት ስጋዋን እየሸጠች በጋለሞታነት የምትኖረዋ ትንሿ እህትህ፡ በጠቅላላው ዘመዶችህ ሁሉ በችግር ስለተበታተኑ ለዚህ ያደረሳቸው መለስ ዜናዊ ቢሆኑም አንተ ወታደሩ ለህዝቡ አለኝታቸው መሆንክን በተግባር ለማሳየት አልፈለክም። የኢትዮጵያ እናቶች አንተንና ጓደኞችህን ወልደው የወላድ መካን ስለሆኑ፤መለስ በጉግ ማንጉጎች ልጆቻቸውን አስገደለባቸው።አንተ ወታደሩ ህዝብህን አለሁልህ የምትለው መቸ ነው?

በህዝቡ ላይ ያለው ችግር ረሃቡ እንግልቱ ስቃዩ እየጨመረ ሲሀድ፣ ያንተም ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ስለሆነ የምታገኘው ደመወዝ በርከት ያለ ቢምስልም፣ የወር ገቢህ ሰባት መቶ ብር ቢሆንም፣ አንድ ኩንታል ጤፍ በሺህ ሁለት መቶ ብር ገዝተህ ለመኖር አትችልም ሰላማዊው ህዝብ ምንም ገቢ ስለሌው ቁርስ በልቶ ምሳና እራት የለውም፣ አንተ ወታደሩ ይህንን ስትመለከት አይቆጭህም አንጀትህ አያርም? ዘረኛው መለስ ህዝቡን በጎሳ ከመከፋፈሉ ሌላ አንተን ወታደሩን አማራ ኦሮሞ ከምባታ እያለ ሰላአገለለህ፣ እንደህዝቡ አንተም እንደቅኝ ተገዥ በሁለተኛ ደረጃ የምትተዳደር ስለሆንክ ይህ ግፍ ይህ ውርደት ይህ ንቀት አያስቆጣህም? በጎሳህ ምክንያት የውትድርና ማእረግ ሹመት ተከልክለህ በታዛዥነት ስታገለግል፣ አገርህን በማይመለከት ጦርነት ተልከህ ሱማሊያ ውስጥ ስትሞት፣ አስከረንህ በገመድ እየተጎተተ በድንጋይ ስትደበደብ ውሾች ሲጫወቱብህ ሰላስና አርባ የምትሆነው በአንድ ጉርጓድ ትቀበራለህ፣ መሞትህ ለዘመዶችህ አይነገርም፣ ከዘመትከው ወታደር ስንቱ እንደሞተ ስንቱ እንድቆሰለ ባአህዝ መለስ እንዲነግራችው ምክር ቤትህ ቢጠይቁት፣ ይህንን ለማውቅ መማክርቱ አያስፈልጋቸውም እኔም ለመናገር አልገደደም የሚል መልስ በንቀት ነገራችው፣ መለስን ለጠቅላይ ሚኒስትር የመረጡት የምክር ቤት አባላት ሲሆኑ፣ በአባላቱ ላይ ያለው ንቀት አስከዝህ ድረስ ስለሆነ አንተ ወታደሩ የመለስ ታማኝ አገልጋይ መሆንህን በተግባር ስለአሳየህ፣ ሳትሞት ሞተሀል፣ መለስ አንተን ወደሱማሊያ ልኮ ያስገደለህ ከአሜሪካ መንግስት ገንዘብ ለማግኘት ስልሆነ፣ ወንድሞችህን ጦር ሜዳ አስገድሎ የሰበሰበውን ገንዘብ በውጭ አገር ባንክ ሲያከማች የቀረውን ገንዘብ ከነሱ አብራክ በመወለዴ እኮራበታለሁ ለሚላቸው ለጎሳዎቹ አከፋፍሏል።

መለስ ዘናዊ አገርህንና ህዝብህን በመዳፉ አስገብቶ የፈለገውን ለመስራት ስለቻለ ኤረትራን አስገነጠለ፣ በራሱ እንዝህላልነት ባደርገው ስህተት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከሻቢያ ወታደሮችጋር እንድትዋጉ ሰላአዘዘ ትርጉም ለሌለው ጦርነት ከሁለቱም ወገን ከሰባ ሺህ የበለጡ ዘጎች እንደሞቱ ታውቋል፣ በዚህ ጦርነት ምን ጥቅም ተገኘ? ከዚህ አልፎ የባህር ወደብህን ለሻቢያ ሸለመ፣ ሸቀጡን ማስገቢያ ስላአጣ ሚጢጢ ትንሿ

ጅቡቲ ወደቡን ይዛ ቀንና ለሊት ታልበናለች፣ ጅቡቲ ለእለታዊ ፍጆታ የሚያስፈልጋትን ምግብ የምታገኘው ከኢትዮጵያ ሲሆን፣ ለወደቡ የምንከፍለው 90% ከምንሸጠው ምግብ የምናገኘው ገቢ 10% ብቻ ነው፣ ሰዬ አብርሃና አስራት ገብሩ አሰበን ለሻቢያ ከሸለሙ በኋላ፣ አሁን አሰብን አናስመልሳለ እያሉ ሲያሾፉብን ኢሳይያስ የአሰብን ወደብ ለኢራን መንግስት በከፍተኛ ኪራይ አከራይቶታል፣ መለስ ያልሸጠውያለወጠው ነገር የለም፣ አንተ ወታደሩ በፍራቻ ይሁን በጥቅም ተደልለህ የመለስ ታማኝ በመሆህ የአንተን እንቅስቃሴ ለማየት፣ የአባቶችህን ቅርስ የጀግናው የአጼ ተዎድርስን አገር ቋራን ጭምር አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር ለሱዳን መንግስት መሸጡን ሰምተናል፣ አንተ ወታደሩ ይህንን አሳፋሪ ስራ እየሰማህ ቸል ካልክ፣ መለስ ነገ የቴዎድሮስን አጽም አውጥቶ እንደ ድንቅነች አጽም አሜሪካ ልኮ ገንዘብ ይሰበስባል

ከዚህ ሁሉ ውርደት፣ መናቅ፣ እንግትና፣ ረሀብ የምትገላግለን፣ የተገፈፍነውን መብትና ነጻነት የምትመልስልን፣ ከወገን የቅኝ ገዢ እጅ የምታወጣን. በሁለተኛ ደረጃ የምንተዳደረውን ዘጎች የአገራችን ባለቤቶቶች የምታደርገን አንተ ልጃችን ወንድማችን የኢኢትዮጵያ ወተደር ስለሆንክ ማድረግ የሚገባህን ግዴታ በተግባር እንድታሳየን እንጠይቁሀለን።

የተከበራችሁ አንባቢዎች፣//// መለስ ዘናዊ ከሰስት ሳምንታትት በፊት በ 2002 የሚደረገው ምርጫ ፍትሃዊ ሰላማዊ ስለሆነምርጫውን መካፈል ይኖርባችኋል ብሎን ነበር፣ አሁን በሰሞኑ ደግሞ በቀላጤው በበረከት ሲሞን እንደሰማነው መንግስት በምርጫው ብጥብጥ እንዳይነሳ መከላከል ብቻ ሳይሆን በጥባጮችን አጥብቀን እንቀጣለን በማለት ዛቻና ማስፈራሪያ አሰምቶናል፣ ይህ ሁሉ ችግር ለምንድነው? ተጠቃሚው አንድ ሰው መለስ ዘናዊ ብቻ ስልሆነ፣ ለአንድ ሰው ጥቅም ይህ ሁሉ ፉከራና ማስፈራሪያ ለምን አስፈለገ? የኢትዮጵያ ህዝብ በመርጫው ለመካፈል ፍላጎቱን ሲገልጽ.መንግስት እንድንመርጥ ከፈለገ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ ከምርጫው በፊት ስምንት ነጥቦች በቅድሚያ በተግባ እንዲውሉሉን እንፈልጋለን ብለዋል፣ አምባ ገነኑ መለስ ዜናዊ ይህንን ለመፈጸም ዝግጁ ነው? የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ዘረኛ ገዥ በሰላም ለማስወገድ ሁለት አማራጪች አሉት፣ አንደኛው በአንድ በተወሰነ ቀን ወንድ ሴት ወጣት አዛውንት ሁሉም ተሰብስቦ ሰላማዊ ስልፍ በማድረግ ችግራችንን እናስወግዳለን፣ ይተኮስብኛል የሚል ፍራቻ አያስፈልግም፣ መሞታችን ካልቀረ ተዋርደን ተንቀን ከመሞት፣ በሺህ የምንቆጠረው ደረታችንን ለጥይት ሰጥተን መጋፈጥ ነው፣ ሁለተኛው አማራጭ የመከላከያ ሰራዊታችን እንዳለፈው ጊዜ ስንገደል በዝምታ አይቀመጥም፣ መለስ እንዳለፈው ጊዜ በማስፈራራት ስልጣን ላይ ሊቆይ አይችልም፣ ያለው አማራጭ በርግጎ መጥፋት ወይም ከኛ ጋር መሞት ብቻ ነው።

ከፍራቻ የተነሳ መለስ የግንቦት ሰባትን አባላት መንግስቴን ለመገልበጥ ተነስተዋል ብሎ ከዘላበደ በኋላ የወያኔን መሪዎች ለመግደል የተነሱ ናቸው ብሎ ቀባጠረ፣ ያለማስረጃ በጥርጣሬ የያዛቸውን ተከሳሾችጃ ወደአስር ቤት ላካቸው ከታሰሩት ውስጥ የሰማኒያ አመት አዛውንት ሲገኙ መለስ በዚህ አድሚያቸው የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አባት ማሰሩ ቂምን በቀል ለማስከፈል ሲሆን መለስ ምን ያህል ጨክኝና ፈሪ መሆኑን ራሱ መስክሯል።
ይህንን ጽሁፍ ከመደምደማቸን በፊት አንድ ሃሳብ ሰላለን እናካፍላችሁ፣ መለስ ምንሊክ ቤት መንግስት በገባ ማግስት ሰንደቅ አላማቸንን ጭርቅ ነው በማለት ተሳለቀብን፣ ይህን መሳለቅ በማወቅ ይሁን በፍራቻ አፋችንን ስለዘጋን፣ መለስ በእኛ ሰንደቅ አላማ ጀርባ ሌላ ጨርቅ ሰፍቶበት አዲሱ ሰንደቅ አላማችሁ ይህ ነው ብሎናል፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ድምጻችንን ሳንሰጥበት አላፊ ነርፍ ጠራርጎ ያመጣቸው ዘራፊዎች የኛን ሰደቅ አላማ ለመለወጥ መብት የላቸውም.እኛ በቻ ሳንሆን የትግርራይ ህዝብም

ስለአልተጠየቀ በጋራ ጥያቄያችንን እናቅርብ፣ መለስ እንዳሰበው ይህ ሰንደቅ አላማ ከተለወጠ አባቶቻችን ያፈሰሱት ደምና የከሰከሱት አጥንት ይታዝዘበናል ታሪክም ስለሚፈርድብን በአንድነት እንጠይቅ።

ፍራንክፋርት ሚያዚያ 30 /2001 08፣05፣2009

# የኢትዮጵያ ህዝብ በነፍስ ገዳዩ በመለስ ዜናዊ ላይ
# በጅኖሳይድ ዋች የጦር ፍርድ ቤት የሚያቀርብበት ክሶች






ያም ሆነ ይህ ከአሁን ወዲያ
ዝም ማለት የሚችል ማንም የለም።
ኢዮብ 4. 2